

*በአልማ የተሰራ የሳንጃ ወንዝ ድልድይ (ታች አርማጭሆ)*

የመንገዱ ስራ ሳንጃ ወንዝ ላይ ትልቅ ድልድይ መገንባትና ተንፈል የተሰኘውን አስቸጋሪ ተራራ ሰንጥቆ ማለፍን ይጠይቃል፡፡ አልማ ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት በቂ ማሽነሪዎችን ማስማራቱ አልቀረም፡፡ አልማ ከተበላሹበት ጠግኖ ካንቀሳቀሳቸው ሦስት ዶዘሮች በተጨማሪ አንድ “D8R” በጣም ትልቅና አዲስ ካተር ፒላር ዶዘር፤ አንድ ግሬደር፤ አንድ ሎደር፤ሦስት አዳዲስ ኒሳን ፒካአፕ መኪናዎች፤ ገልባጮችና አለትን ማፈንጃ ቲ ኤን ቲ ነበሩት፡፡

አልማ የቱንም ያህል የሥራ መሳሪያና ሞያተኛ ቢያስፈልፍም፤ ብዙዎች ግን “አልማ መንገዱን ይስራዋል” ብለው አላመኑም፡፡ የሃይማኖት መሪዎችና ታዋቂ የአገር ሽማግሌዎች ሳይቀሩ “ሜዳ ሜዳውን ይሮጣሉ እንጅ ፈተናው ተንፈል ተራራ ላይ ነው፡፡ ሙገር አያሳልፋቸውም” ሲሉ በእርግጠኝነት ተናገሩ፡፡

ሙገር የአገሬው ሰው የሚያምንበትና በተንፈል ተራራ ላይ የነገሰ ቆሌ ነው፡፡ በዚህም “ለሙገር ደም ካልፈሰሰለት መንገድ የሚሰሩት ማሽኖች አያልፉም” ተባለ፡፡

ከሳንጃ ከተማ እስከተንፈል ዳገት ግርጌ ድረስ የመንገድ ስራው አልጋ በአልጋ ነበር፡፡ የአልማ ሠራተኞች ተንፈል ተራራንም እያረሱት የተወሰነ ርቀት ድረስ ሄዱ፡፡በመጨረሻ ግን አንድ አስቸጋሪ ቦታ ላይ ደረሱና ዶዘሩና ኦፕሬተሩ ስቃይ በዛባቸው፡፡ ብዙ ተደክሞም አስቸጋሪውን ቦታ ለማሸነፍ አልተቻለም፡፡ ዶዘሩም ተበላሽቶ ቆመ፡፡

ይህን አይቶ ”እኛም ብለን ነበር” ያላለ የለም፡፡ ”ይኸው የአልማ ሞተር ዓይኑ ጨለመ (መብራቱ ጠፋ)፤ ታንፋሹ ቆመ (ሞተሩ ጠፋ)” ተባለ፡፡ ዶዘሩን የገታው ሙገር መሆኑ ታምኖ ምሱ እንዲቀርብለት ትዕዛዝ የሚመስል ማሳሰቢያ የሚሰጠው ተበራከተ፡፡ የአልማ ሠራተኞች ግራ ተጋቡ፡፡ ከመካከላቸው ዶዘሩን ያቆመው ሙገር መሆኑ ላይ ያመኑም ነበሩ፡፡ የፕሮጀክቱ ኃላፊ ወደ አልማ ዋና ጽ/ቤት ባሕር ዳር ሄዱ፡፡ ለሙገር ሰንጋ ይጣልለት ዘንድ ፈቃድ የተጠየቀው የአልማ ጽ/ቤት ጉዳዩ አስገራሚ ሆነበት፡፡ የማህበሩ ሊቀመንበር ግን ሰንጋ በሬ ቀርቶ የዶሮ ጫጩትም እንዳይታረድ ፤ የተሰበረው የዶዘር ዕቃ ግን በአስቸካይ ከአስመጪው ኩባንያ እንዲገዛ ትዕዛዝ ሰጡ፡፡

ከዚህ በኋላ ዶዘሩ ተጠግኖ እንደገና ለሥራ ተሰናዳ፡፡ ዶዘሩ አስቸጋሪውን ቦታ ያሸንፈው ሲጀምር ግን የሙገር አማኞች ”ሙገር በአካባቢው አልነበረም፤ ሚስቱን ሊጠይቅ ወደሉላ ቦታ በሄደበት አጋጣሚ ነው ተንፈል የተደፈረው” ሲሉ ማስተባበያ ሰጡ፡፡ እናም ተንፈል እጁን ሰጥቶ ከሳንጃ ማሰሮ ደንብ የሚያደርሰው መንገድ ተጠናቀቀ፡፡

ታች አርማጭሆ በሰሜን ጎንደር ከሚገኙት ወረዳዎች ከቋራ ቀጥሎ ሁለተኛው ሰፊ ወረዳና መሬቱም ለም ቢሆንም፣ ተፈጥሮ የቸረችውን ፀጋ ለመጠቀም የታደለ አልነበረም፡፡ ያለፉት መንግሥታት ፀጥታውን የሚያውኩ ጠንቆች ስለሆኑበት፣ አንዴም በሙሉ ቀልቡ ወደምርት ሥራ የተሰማራበት ዓመት የለም፡፡ በአንድ እጁ እርፍ በሌላው ጠመንጃ ይዞ በከፊል ገበሬነትና በከፊል ወታደርነት መኖሩ፣ አብዛኛው ለም መሬቱ ጦም አዳሪ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

በአጠቃላይ፣ የትምህርትና የጤናም ሆነ ሌሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት ከሚሰጡ ተቋሞች ጋር ሳይተዋወቅ፣ ድፍን ወረዳው ገጠር እንደሆነና በዛፍ ሥር እየተገበያየ ከከተማ መልክ ሳይተዋወቅ የኖረበት የጨለማ ዘመን ያከተመው የአሁኑ መንግሥት አካል ከሆነና አልማ መንገዱን ከሰራው በኋላ ነው።

በአሁኑ ጊዜ ታች አርማጭሆ የተኛ ሃብቱን ከእንቅልፉ ቀስቅሶ ይጠቀምበት ጀምሯል። አልማ የቀደደውን ትልቅ መንገድ ተከትለው ወደ ሁሉም የወረዳው ቀበሌዎች የሚያደርሱ የገጠር መንገዶች ተሠርተዋል። ማንኛቸውም የመንግሥት መዋቅሮች ተዘርግተዋል። የትምህርት፣ የጤና፣ የውሃ፣ የመገናኛና የመሳሰሉት አገልግሎቶችና መሠረተ ልማቶች እየተስፋፉ ነው። በወረዳው ውስጥ በርካታና አዳዲስ ከተሞች ተቆርቁረው በማደግ ላይ ይገኛሉ። ወረዳው ሰሊጥ፣ ጥጥና እጣንን በመሰሉት የገበያ ምርቶች ሥመ-ጥር የሆነበትና በመቶዎች ሚቆጠሩ የግል ባለሃብቶች ሰፊ መዋዕለ ነዋይ የሚያፈሱበት የሲሳይ ምድር ለሆነበት ዘመን በቅቷል።

ይህ ነው አልማ የሰራውን የሳንጃ ማሰሮ ደንብ መንገድ ልዩ የሚያደርገው። የተነጠለን ከአገር ያዋሃደ፣ የተረሳን ያስታወሰ፣ የተኛ ሃብትን የቀሰቀሰ... መንገድ መሆኑ ነው ፋይዳውን እጅግ በጣም ትልቅ የሚያደርገው። ዛሬ መንገዱን ተከትሎ ሁሉም መልካም ነገር ወደ ታች አርማጭሆ ይሄዳል፣ ሁሉም መልካም ነገር ከታች አርማጭሆ ይመጣል።





የተንፈል ዳገት (ታች አርማጭሆ)

## 2. ከሮብ ገበያ ድጎ ፅዮን

አብዛኛዎቹ የጎጃም ወረዳዎች በደርግ ዘመነ መንግሥት በመኪና የሚደረስባቸው እንደነበሩ ይነገራል። መንገዶቹ የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ ይሁኑም አይሁኑም፣ ወንዝ እያሻገሩ የማዶ ለማዶውን ማገናኘታቸውን፣ ከጋማ ከብትና ከሰው ትከሻ ሸክም መገላገላቸውን በማሰብ ብቻ "እሰየው" እንላቸው ይሆናል ።

ቢቡኝ ጎጃም ውስጥ ከሚገኙት ወረዳዎች አንዷ ነች። ቢቡኝ ‹‹ከሰው ሰው ቢለዩ፣ ላመትም አይቆዩ›› ይሉትን አባባል ታስታውሰናለች። ይህን



የአልማ ማሽነሪዎች በሳንጃ-ማሰሮ ደንብ
መንገድ ሥራ ላይ
(በሰተጀርባ) ተንፈል ተራራ

የሚያስታውሰን ‹‹ከብዙዎቹ የጎጃም ወረዳዎች ተለይታ ለምን መኪና መንገድ ሳይሰራላት ቀረ?›› የሚል ጥያቄ ሲነሳ ነው።

ምክንያቱ ትርፍ አምራች ወረዳ አለመሆኗ ነው። ሌሎቹ ግን ከራሳቸው ፍጆታ አልፎ ለሌላው የሚተርፍ ምርት ማምረት በመቻላቸው የመኪና መንገድ ‹‹ሊሰራላቸው›› ቻለ። ምናልባት ለትርፍ አምራችነታቸው የተሰጠ ማበረታቻ ወይም ሽልማት ይሆን? ትርፍ አምራች ያልሆነችዋን ቢቡኝ የሚያስረሳ ሌላ ምን ምክንያት ሊኖር ይችላል?

ይህን ጉዳይ መነጋገሪያ የሚያደርገው አብዛኛዎቹ ወረዳዎች በመንገድ እንዲገናኙ መደረጋቸው የሚያስወቅስ ስለሆነ አይደለም። በደፈናው ካሰላነው፣ የአንዷ ወረዳ ብቻ መዘለል ኢምንት ሆኖ ይታየናል። በዚያን ጊዜ በአማራ ክልል የሚገኙ የሸዋ፣ የጎንደርና ወሎ አካባቢዎች በርካታ ወረዳዎቻቸው መንገድ አልነበራቸውምና።

ልናነሳ የፈለግነው ከመንገዶቹ መሠራት በስተጀርባ የነበረው እውነታ ልማት ሳይሆን ጥፋት መሆኑን ነው። "መንገዶቹ ለጎጃም ሕዝብ ተሰሩ" ከማለት ይልቅ፣ "ለእርሻ ሰብል ገበያ ድርጅት (እሰገድ) ተሰሩ" ቢባል ትክክል ይሆናል። የደርግ መንግሥት ትርፍ አምራች ከሆኑት ቀርቶ ካልሆኑትም ራሱ በሚጥልባቸው መጠንና ርካሽ ዋጋ እህል እንዲሸጡለት ያስገድዳቸው እንደነበር ይታወቃል። ከመዝረፍ ያልተለየውን ምርት አስገድዶ በርካሽ ዋጋ ለመውሰድም፣ በተለይም ትርፍ አምራች ወደሆኑት አካባቢዎች የሚያስገቡ መንገዶችን መሥራት ነበረበት።

በዚህ ዓይነት ሲገመገም፣ የጎጃም ወረዳዎች መንገድ የተሠራባቸው እንጂ የተሠራላቸው እንዳልነበሩ እንረዳለን። "መንገድ መሠረተ ልማት ነው" የሚባለው፣ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት ቅድመ ሁኔታ በመሆኑ ነው። ወደ ኋላ የቀሩ አካባቢዎች በመንገድ ሲገናኙ መንገዱን ተከትለው ትምህርትና ጤና ይስፋፋሉ፣ ለምርታማነት የሚበጁ ነገሮች ሁሉ በቀላሉ ይደርሳሉ፣ የገበያ ግንኙነት ይፈጠራል። በቀድሞው መንግሥት ለእርሻ ሰብል ገበያ ድርጅት የእርካሽ ሸመታ ተብለው የተሰሩ መንገዶች ግን የዚህ ተቃራኒ ነበሩ። እነዚህ መንገዶች የግብርና ልማት፣ የጤና፣ የትምህርትና መሰል አገልግሎቶችን የሚያደርሱ ሳይሆኑ፣ አርሶ አደሩ በራሱ ጥረት ያፈራውን ምርት በወደቀ ዋጋ ነጥቀው የሚመለሱ እንደበሩ ከማንም የተሰወረ አይደለም።



ቢቡኝ ወረዳ መንገድ የተነፈጋትም የመንገድ ስራው ዓላማ ላልለሙት አካባቢዎች የልማት መሠረት መጣል ስላልነበረና እሷም ይዘርፏት ትርፍ አምራች ስላልነበረች ነው፡፡ እንጂ፣ ወደ ወረዳዋ ዘልቆ ለመግባት አስቸጋሪውን የጮቄ ተራራ ሰንጥቆ ለማለፍ ብዙ ድካም የሚጠይቅ በመሆኑ አይደለም፡፡

አሁንም፣ ፈታኙን የጮቄ ተራራ እየናደ መንገድ መስራቱ አልማን በግርምታ ዓይን እነድንመለከተውና ፅናቱን እድናደንቀው ይገፋፋን ይሆናል፡፡ ይህን ሃቅ ባንክደውም፣ የዚህ መንገድ ቁምነገር የሚመዘነውም እጅግ ወደ ኋላ ቀርቶ ለነበረው ወረዳ ዘለዓለማዊ የልማት መሰረት የጣለ በመሆኑ ነው፡፡ አልማ የሠራው የሮብ ገበያ ድጎ ፅዮን መንገድ ቢቡኝ ወረዳ በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት ጎዳና መራመድን ያስጀመራት የልማት በር ከፋች መሆኑን ራሱ የወረዳው ሕዝብ ይመሰክራል፡፡ ‹‹ትምህርትና ጤና በመንገድ አርገህ ና!›› እያለ ይቀኛል፡፡

## 3. የእንጭቄ ወንዝ ድልድይ

እንጭቄ ወንዝ በሰሜን ወሎ ዞን ዋድላ ወረዳ የሚገኝ ወንዝ ነው፡፡ ኮንና የኔንጃ የተሰኙ ቀበሌዎች ኩታ ገጠም ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለት የዋድላ ወረዳ ቀበሌዎችን የሚያዋስነው ረባዳማ መሬት ውስጥ ደግሞ እንጭቄ ወንዝ አለ፡፡

ቡና የሚያጣጣ ጉርብትናቸው የኮንና የኔንጃ ቀበሌዎች ነዋሪዎችን ሰርክ ያገናኛቸዋል፡፡ ይህ ባይሆንም፣ በሳምንት አራት ቀን የሚያገናኛቸው አንድ የማይታለፍ ጉዳይ አለ፡፡ በሳምንት ሁለት ቀን ኮን ላይ ገበያ ነው፣ በሳምንት ሁለት ቀን ደግሞ የኔንጃ ላይ፡፡ ሰው ከተጎራበተ፣ በገበያ ከተገናኘ፣ ለደቦ በጋራ ከተሰለፈ፣ የዕለት ተዕለት ደስታና መከራውን ከተካፈለ ‹‹የአገሬ ልጅ፣ የወንዜ ልጅ›› መባባሉ አይቀርም፡፡



ውሃ ሊቀዱ፣ ከብት ሊያጠጡ፣ ልብሳቸውን አጥበው ገላቸውን ሊለቃለቁ የሚገናኙበትና በውሃ እየተራጩ የሚጫወቱበት ወንዝ የፍቅርና የአንድነት ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል። ወንዝ ፍቅርና አንድነት ከሆነ፣ እንጭቄም ለኮንና ለየኔንጃ ቀበሌዎች የፍቅርና የአንድነት ምሳሌያቸው መሆኑ ነው።

ዛሬ ነገሩ ሁሉ ተለውጦ ሊሆን ይችላል፣ቀደም ሲል ግን እንጭቄን ‹‹ጭንቅ›› እንጂ ‹‹ፍቅርና አንድነት›› ሲሉት አይደመጡም ነበር። እንጭቄ በጋውን ተኝቶ እየከረመ ክረምት ላይ ግን የሚፎገላ፣ በዓመት ከሰባት ያላነሰ ሰው ካልወሰደ ምሱ የማይሞላለት፣ በርካታ ንብረታቸውንና የቤት አንስሳትን ያስገበራቸው ደመኛቸው መሆኑን ይናገራሉ።

ይሸጡትና ይገዙት ቢኖራቸውም፣ እንጭቄ ሰቆቃ እየሆነባቸውና የእንጀራ ገበያቸውን እያስተጓጐለባቸው "እንጀራ አይውጣልህ" ሲሉ ረግመውታል። ነጋዴን ከነጭነቱ፣ ገበሬውን ከነሞፈር ቀንበሩ እያስቀረ መራር ለቅሶ ያስለቀሳቸውና የቤት አውራ እያሳጣ ለኑሮ መከራ የዳረጋቸው ቤተሰቦችም ብዙ ናቸው። "የአገር ሽማግሌ፣ የነገር አዋቂ፣ የወንዝ አስታራቂ" የሚሏቸውን የበላ ነውና፣ እንጭንቄ ዓይኑን ለአፈር ሲመኙለትና የቂም ጥርስ ሲነክሱበት የኖረ ወንዝ ነው።

እጭንቄን የሚገስፅውና የሚመክረው፣ በገዳይና በሟች መካከል ሰላም የሚያወርድ ብልሃተኛ ባገር ጠፍቶ በኮንና በየኔንጃ ነዋሪዎች ላይ የደረሰው የአያሌ ዓመታት መከራ ዛሬ ግን ትዝታ ሆኗል። ሁሉም ገላውን ሰዶ እንጭቄን ይረማመድበታል። እግረኛው በእግሩ ፈረሰኛው በፈረስ ይሻገረዋል። ቀደም ሲል እንጭቄ በኮንና በየኔንጃ ሰዎች በላያቸው ላይ ይሄድ ነበር። ዛሬ ግን የኮንና የኔንጃ ሰዎች እንጭቄን በላዩ ላይ ይሄዱበታል። በላዩ ላይ ከብት ይነዱበታል። ወንዙና ወንዘኞቹ ታርቀው ሰላም ወርዷል።

በወንዝና በወንዘኞቹ መካከል ሰላም ያወረደው፣ የነገር አዋቂውና የወንዝ አስታራቂው ደግሞ አማራ አቀፍ ልማት ማህበር (አልማ) ነው። አልማ በ1994 ዓ.ም እንጭንቄን የሚያሻግር ድልድይ ከሠራ ወዲህ አማን በአማን ሆኗል። እንጭቄ ምንም እየጎፈላ ቢዘልና ቢንጠራራ 12 ሜትር ከፍታ ያለውን ድልድይ አይደርስበትም። ባለ 3.7 ሜትር ወርድ ድልድዩ ከኮን ቀበሌ እስከ የኔንጃ ቀበሌ የተዘረጋ ቁመቱ ሲለካ 32 ሜትር ይሆናል። 64 ክንድ ማለት ነው።

ስድሳ አራት ክንድ የሰማይና የምድርን ያህል እንደራቀ የዋድላ ሰዎች እስከ 1994 ዓ.ም ድረስ ሳይገናኙ ያሳለፏቸውን ክረምቶች ቁጠሯቸው። እርግጥ ነው፣ ድልድዩ 338,335 ብር በልቷል። ይህን ከበላ ወዲህ ግን ሰው አልበላም። ቅን ልቦና ይዞ፣ ቅን መንገድ ተከትሎ ለሠራው መንገድ ትምህርትና ጤና የሚመጡበት ጎዳና ብቻ አይደለም፤ ሕይወትም ነው።

# ጋዜጠኞች ስለ አልማ

## ጋዜጠኛ አንሙት አብርሃም

## ከኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት



አልማ የህዝብ፤ ህዝቡን አስተባብሮ ለህዝብ የሚሰራ፤ የድህነትን ክፋት የተገነዘበ፤ መፍትሔውም ሥራና ሥራ መሆኑን ያወቀ ጠንካራ ድርጅት ነው። ያልተደረሱትን በመድረስ በክልሉ ጠረፋማ አካባቢዎች ተራራና ገደል ሳይገድበው የሚያከናውናቸውን የልማት ሥራዎች አይቻለሁ። በትምህርትና ጤና ተቋማት ግንባዉታ እንዲሁም በተዋልዶ ጤና አገልግሎት ትልቅ እመርታ አስመዝግቧል።

የብዙ የልማት ፕሮጀክቶችና ግብረሰናይ ድርጅቶች ውስኑነት ሆኖ የሚታየኝ ወደ ታችኛው የህብረተሰብ ክፍል ወርዶ ህዝብን ያሳተፈ ሥራ አለመስራት ነው። አልማ በዚህ አይታማም። መንገድና መሰል መገናኛ አውታሮች በሌሉበት ድንጋይ በግመልና በሰው ኃይል እየተጓጓዘ የትምህርትና የጤና ተቋማትን በደጃፋቸው ያገኙ ነዋሪች እንባ እየተናነቃቸው ያሉኝን አልረሳውም።

እናም፤ ደራሽነትና አሳታፊነት የአልማ መለያዎች ናቸው። በሀገራችን ምሳሌና አርዓያ የሚሆን ሀገር በቀል ግብረ ሰናይ ድርጅት ነው። የበለጠ የአልማ ራዕይ ተሳክቶ እንድናይ የሁላችንም /ተወላጆችና ደጋፊዎች/ አስተዋጽኦ ያስፈልገዋል። አይዞህ ማለት ከእንቅፋት ያድናል።

# ጋዜጠኛ ዘመነ ዮሐንስ

# ከሬዲዮ ፋና



እንዲህ መኪናው ዳገቱን መውጣት እያቃተውና ወደ ኋላ እየተንሸራተተ/ ስትራኝ እያደረገ/፣ በታኮ እየቆመ የሚሄድበትን መንገድ አልማ እየተሻገረ ይሰራል ብዬ አስቤ አላውቅም:: በጋዜጠኝነት ህይወቴም ልረሳው የማልችለውን ሥፍራ ጉብኝቻለሁ :: የሰሜን ሸዋ ግሼ ራቤል መንገድና ርቀቱ ሲገርመኝ፣ የቦሰና ቀበሌ /ደቡብ ወሎ ዞን ቃሉ ወረዳ የምትገኝ ቀበሌ /መንገድ ደግሞ አስደንቆኛል:: በእርግጠኝነት የምናገረው ደግሞ መንግስት ካለው የሰው ኃይልና የገንዘብ አቅም አንፃር ርቆ ገብቶ እንደ ቦሰና ዓይነት ቦታዎችን ያዳርሳል ብዬ አላስብም:: ይልቁንም እንደ አልማ አይነት የልማት ደጋፊ ማህበራት እንዲቋቋሙ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ክፍተቶችን እንዲሞሉለት መደረጉ ተገቢነት አለው:: አማራ አቀፍ ልማት ማህበርም የክልሉን ነዋሪዎች መሠረታዊ ችግሮች ለመፍታት እንደ ጤናና ትምህርት ተቋማት የመሰሉትን ለመገንባት ጋራ ወጥቶና ቁልቁለት ወርዶ እየሠራ አለኝታ የህዝብ ማህበር መሆኑን በጉብኝቱ ተገንዝቤአለሁ::

የጋዜጠኞች ቡድን ለመጀመሪያ ጊዜ ሄደንበት ያስፈራንን መንገድ የአልማ ባለሙያዎች ግን ምን ያህል እንደተመላለሱበት ሳስብ ለሥራው ያላቸውን አክብሮት አሳይቶኛል::
እጅግ የገረመኝ ነገር ቢኖር የቦሴ ጤና ኬላ በሚሰራበት ወቅት ጋራው መኪና ስለማያስገባና ጥርጊያ መንገድ ስላልነበረው የግንባታ ዕቃው በሰውና በግመል ጀርባ ተመላልሶ መጠናቀቁን ስሰማ ነው:: ሥራው ካለቀ በኋላም ቢሆን መኪኖች ግራ ቀኝ እየተወዛወዙ የኮረት ድንጋዩ ጉማቸውንና መሪያቸውን እየፈተነ፣ ሲያሻቸው ወደ ኋላ እየተንሸራተቱ በእግርና በእጅ ፍሬን እየተገቱ በጭንቅ በአሣር የቦሴን ጤና ኬላ ጉብኝተው መመለሳቸውን በማየቴም ደስተኛ ነኝ::

አንድ ነገር ግን ማለት ከተፈቀደልኝ፣ አልማ እንዲህ የአገር ጫፍ ከመሰሉ ቦታዎች እንደሚደርስ እስካሁን ያለማወቁ ከእኔ ወይስ አልማ ራሱን በሚገባው ሁኔታ ካለማስተዋወቁ የመነጨ ይሆን? በጥያቄ ይያዝልኝ:: እኔ የአልማን አጠቃላይ እንቅስቃሴ የተረዳሁት በሰሞኑ የመስክ ጉብኝት ነው ማለት እችላለሁ:: በደቡብ ወሎና ሰሜን ሸዋ ዞኖች የሚገኙ አርሶ አደሮች ጤና ኬላ

ተሰርቶላቸው ት/ቤት ተገንብቶላቸው ሲያስመርቁ ከፊታቸው የታዘብኩትን ደስታ መቼውንም አልረሣውም፡፡ ከዚህ በኋላም የአማራ ክልል ተወላጆች እንዲሁም የልማቱ ደጋፊዎች በሙሉ ስለ አልማ ያላቸውን ግንዛቤ ለማሳደግና ልማቱ የሚፋጠንበትን ዕድል ለመፍጠር ሙያየን ተጠቅሜ በግሌም ሆነ በሚዲያው የበኩሌን ሚና ለመጫት ቃል ገብቻለሁ፡፡





አልማ በፈታኝ የገጠር መንገዶች እያለፈ ያለማል

# ጋዜጠኛ ይህአለም መለሰ
# ከአማራ ክልል መገናኛ ብዙሃን ኤጀንሲ



አልማ በአማራ ክልል የሚያደርገውን የልማት እንቅስቃሴ በሥራ አጋጣሚ ተዘዋውሬ ተመልክቻለሁ፡፡ ማህበሩ ከበጎ አድራጊ ድርጅቶችና ከአባላቱ የሚያሰባስበውን ገንዘብ በመጠቀም በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች የትምህርትና የጤና ተቋማትን በመገንባት! ለስራ አጥ ወጣቶች የሙያ ስልጠና ሰጥቶ ወደ ሥራ በማስገባት! ረዳት ያጡ ተማሪችዎን በገንዘብ በመደገፍ በኩል ትልቅ ስራ ሰርቷል፡፡

የትምህርትና የጤና ተቋማት ባልተስፋፋባቸው አካባቢዎች ርቀትና የመንገዱ አስቸጋሪነት ሳይበግረው ጥራት ያላቸውና የውስጥ ቁሳቁሳቸው የተሟላላቸው የትምህርትና የጤና ተቋማትን በመገንባት ለክልሉ ህዝብ ያለውን የልማት አጋርነት እያሳየ ነው፡፡

በየወረዳው የሚገኙ አባላቱም ወርሃዊ መዋጮ በማሰባሰብ በየአካባቢያቸው ያሉትን ክፍተቶች እንዲሞሉና በአካባቢያቸው ልማት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ እያደረገ መሆኑን ተገንዝቤያለሁ፡፡ በተለይ በደብረ ኤልያስና በሁለት እጁ እነሴ ወረዳ እንደተመለከትሁት ማህበሩ የክልሉን ተወላጆችና ደጋፊዎችን በማስተባበር በርካታ ስራዎችን በመስራት ላይ ነው፡፡

ከክልሉ ውጪ የሚኖሩ አባላቱና ደጋፊዎቹ በያሉበት ገንዘብ አሰባስበው ለዋናው መ/ቤት እንዲልኩ ከማድረግ ባሻገር የሰበሰቡትን ገንዘብ በሚፈልጉት ቦታ ላይ ተገኝተው የትምህርት ተቋማትን እንዲገነቡ፤ በአልማ የተሰሩ የልማት ሥራዎችን እንዲመለከቱና በክልሉ ያሉ ችግሮችን እንዲረዱ በማድረግ ረገድ ያደረገው ጥረት የሚያስደስት ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡

በአሁኑ ጊዜ የክልሉን የትምህርትና የጤና ተቋማት እጥረት ለማቃለል ታላቅ የገቢ ማሰሳበቢያ ኘሮግራም ቀርፆ መንቀሳቀሱ ለክልሉ ልማት መፋጠን ያለውን ቁርጠኝነት ያሳያል ብዬ አምናለሁ፡፡

# የአልማ የልማት ፍፃሜዎች (1984 - 2001)፣ ማጠቃለያ

አልማ ባለፉት 18 ዓመታት በተለያዩ የልማት ዘርፎች ማለትም በትምህርት፣ በጤና ፣በሙያ ስልጠና፣በግብርናና በተፈጥሮ ኃብት ልማትና ጥበቃ፣ በመንገድ ግንባታና በሌሎች መስኮች በርካታ ተግባራትን አከናውኗል፡፡ እነዚህ ተግባራት የአርሶ አደሩን የነፃ የጉልበትና የሞያተኞች አስተዋጽኦ ዋጋ ግምት ሳያካትት ከ500 ሚሊዮን ብር በላይ ጠይቀዋል፡፡ አልማ ለእነዚህ ፕሮጀክቶት ማስፈፀሚያ ያዋለውን ሀብት ያሰባሰበው ከአባላቱ መዋጮ፣ከክልሉ ተወላጆችና ከሌሎች ልማት ወዳድ ኢትዮጵያውያን፣ ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ግብረሰናይ ድርጅቶች ሲሆን እነዚህ የልማት ተግባራትም እንደሚከተለው ተጠቃለው ቀርበዋል፡፡

አልማ ለእነዚህ ውጤቶቹ መሳካት ድጋፍ ያደረጉለትን ወገኖች በሙሉ ምንግዜም ያከበራቸዋል ! ያመሰግናቸዋልም፡፡

## 1. በትምህርት መስክ

1.1. 103 ት/ቤቶች ተገንብተዋል፣
1.2. 112 መደበኛ ያልሆኑ የህፃናት የትምህርት ማዕከላት ተቋቁመዋል
1.3. 7 ቤተ መፃህፍት ተገንብተዋል
1.4. ከ1 ሚሊዮን በላይ መፃህፍት ለትምህርትና የምርምር ተቋማት ተሰራጭተዋል
1.5. ከ19 ሺህ በላይ የጎልማሶች ተግባር ተኮር መሠረታዊ ትምህርት አግኝተዋል
1.6. በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ 120 ልጃገረዶች የ2ኛ ደረጃ እና 60 ህፃናት ደግሞ የ1ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ድጋፍ አግኝተዋል
1.7. 3 መለስተኛ የመምህራን ኮሌጅ የማስደግ ሥራ ላይ የገንዘብ አስተዋጽኦ አድርጓል፣

## 2. በጤና መስክ

2.1. ከ84 በላይ ጤና ኬላዎችና ክሊኒኮች /ታዳጊ ጤና ጣቢያዎች/ ተገንብተዋል
2.2. ከ23.5 ሚሊዮን ብር በላይ ዋጋ ያላቸው የሆስፒታል ቁሣቁስና መሣሪያዎች ለክልሉ የተለያዩ ሆስፒታሎች ተከፋፍለዋል
2.3. በ112 ወረዳዎች የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ፕሮግራም ተግባራዊ አድርጓል፡፡ በልዩ ልዩ ወረዳዎች የህይጅን፣ የሳኒቴሽንና የወባ መከላከል ስራዎች ተሰርተዋል በባህር ዳር ከተማ 20 የጋራ መፀዳጃ ቤቶች ተገንብተዋል
2.4. 2,891 የህብረተሰብ አቀፍ ጤና ወኪሎች ሥራ ላይ ይገኛሉ
2.5. ከ10 ሚሊዮን በላይ የሆኑ ሰዎች የተቀናጀ የቤተሰብ ጤና አገልግሎት አግኝተዋል
2.6. ከ1 ሚሊዮን በላይ አዲስና ከ2.4 ሚሊዮን በላይ ነባር ደንበኛ እናቶች የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት አግኝተዋል
2.7. 124 የፊስቱላ ተጎጂ እናቶች ሕክምና አግኝተዋል
2.8. 4,911 እናቶች ኤች አይ ቪ /ኤድስ/ ቫይረሱ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ አገልግሎት አግኝተዋል፡፡
2.9. 10 ሺዎች የኤች አይ ቪ ምርመራ ተድርጐላቸዋል
2.10. 11,198 ሰዎች ለአባላዘር በሽታ ሕክምና ወደ ተቋም ተልከዋል
2.11. 56 ከት/ቤት ዉጪ እና 40 በት/ቤት ውስጥ ፀረ ኤድስ ክበባት ተቋቁመዋል
2.12. ከ150 ሺ. ላላነሱ ወጣቶች የሕይወት ክህሎት ስልጠና ተሰጥቷቸዋል

## 3. በመሰረታዊ ሙያ በመልሶ መቋቋምና ስልጠና

3.1. 485 የግብርና ባለሙያዎች ሰልጥነዋል
3.2. ከ7,000 ያላነሱ ወጣቶች በተለያዩ የኮንስትራክሽን ዘርፎች፣ በሞተር ኦፕሬሽን፣ በኮምፒዩተርና በሌሎች መሰረታዊ ሙያዎች ሰልጥነዋል
3.3. በባህርዳር ከተማ 40 የጎዳና ላይ ሱቆች ተሰርተዋል
3.4. የሴቶችን የሥራ ጫና ለማቃለልና ሥራ እጥ ወገኖችን ለመደገፍ በተለያዩ ወረዳዎች ከ38 በላይ ወፍጮዎች ተተክለዋል
3.5. ከ1,500 ያላነሱ ብስክሌቶች ለወጣቶች በገቢ ምንጭነት እንዲያገለግሉ ተከፋፍለዋል

## 4. መንገድ ዘርፍ

4.1. 16 ኪ.ሜ የመንገድ ጥገና በሰሜን ጐንደር ዞን ከደባርቅ ሳንቃ በር (ሰሜን ፓርክ)
4.2. 1.6 ኪ.ሜ ከጢስ ዓባይ ከተማ እስከ ጢስ አባይ ድልድይ (ምዕራብ ጐጃም)
4.3. የ53 ኪ.ሜ መንገድ ከሮብ ገበያ ድጐ ጽዮን (ምሥራቅ ጐጃም)
4.5. 42 ኪ.ሜ ርዝመትና በሳንጃ ወንዝ ላይ ከ38 ሜትር በላይ ርዝመት ያለው ድልድይ የተገነባለት የሳንጃ ማሰሮ ደንብ መንገድ (ሰሜን ጐንደር)
4.6. 18 ኪ.ሜ ከድልቢያ ቅዳሚት መንገድ (ዋግ ኽምራ)
4.7. 32 ሜትር የኮን የኔጃ ድልድይ (ወድላ - ሰሜን ወሎ).

## 5. የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ

5.1. ለጐንደር ከተማ የመጠጥ ውሀ አገልግሎት የተገነባው የአንገረብን ግድብ ከደለል አደጋ ለመከላል ከ9,000 ሄክታር በላይ ስፋት ባለው ተፋሰስ ላይ የአፈር ጥበቃና የደን ልማት ሥራ ተከናውኗል
5.2. 12 የችግኝ ጣቢያዎች ተቋቁመዋል

## 6. ሌሎች

6.1. 800 ሺህ ብር የሚያወጣ የእሳት አደጋ መከላከያ መኪና ለባህርዳር ከተማ አበርክቷል

# ምስጋና



የትውልድ ሃገሬ ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ሃብት ክምችት የታደለች፤ በከርሰ ምድሯ እምቅ ሃብቶችን አቅፋ የያዘች፤ የታዋቂ ወንዞችና ሐይቆች እንዲሁም የለም አፈር ባለቤት የሆነች ምድር ናት።

ዓላማዬም ሆነ ምኞቴ ይህቺ አገር አድጋና በልጽጋ የተፈጥሮ ሃብቷ በአግባቡ ጥቅም ላይ ውሎና ዜጎቿም ሠርተው እንዲጠቀሙ ነው።

ዶ/ር ሼክ መሐመድ ሁሴን አል-አሙዲ



# ምስጋና

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

የአማራ ክልል ተወላጅ ባለሃብቶች

ኢትዮጵያውያን ባለሃብቶች

መከላከያ ሠራዊት

ፌደራል ፖሊስ

የአልማ አባላት

ትግራይ ልማት ማህበር (ትልማ)

የኦሮሚያ ልማት ማህበር (ኦልማ)

ደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ልማት ማህበር (ደኢ.ህልማ)

የአማራ መልሶ መቋቋምና ልማት ድርጅት (አመልድ)

አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም (አብቁተ)

MIDROC Ethiopia Plc.

Packard Foundation

Pathfinder /USAID

CORHA/SIDA

Engender Health

Intra Health

DSW

L10K/JSI

UNFPA

# Acknowledgement

/WW/EC

/WW/BIG-LOTTERY

AED/USAID

PACT Ethiopia

Action Aid Ethiopia

French Embassy

A Glimmer of Hope

Save the Children Denmark/SCD

American Embassy

I-TECH (Washington University)

Oxfam-GB

UNDP

GTZ

Norwegian Church Aid

APS (an Italian NGO)

Japan Embassy

British Embassy

(ECDC) Ethiopia Community Development Council

Book Aid International

Rotary Club

CRDA

ESRDF

# የአለማ ጠቅላላ ጉባኤና የስራ አስፈፃሚ ቦርድ አመራር አባላት

# Executive Members of ADA General Assembly(GA) & the Board


ዶ/ር አሰፋ ገብሬ፣ የጠ/ጉ ዳ/ሊቀመንበር
Dr. Assefa Gebre, GA D/Chairman


ዶ/ር ከበደ ታደሰ፣ የጠ/ጉ ሊቀመንበር
Dr. Kebede Tadesse, GA Chairman


ስማቸው ንጋቱ፣ የጠ/ጉ ፀሃፊ
Semachew Negatu, GA Secretary


ጥላዬ ጌቴ፣ ም/ሊ/መንበር
Tilaye Gete, Vice Chairman


ህላዌ ዮሴፍ፣ የቦርድ ሊቀመንበር
Helawe Yosef, Chairman


ሰለሞን ታደሰ፣ ዳይሬክተርና ፀሐፊ
Solomon Tadesse, Derector & Secretary


ብርሃን ኃይሉ፣ የቦርድ አባል
Birhan Hailu, Board Member


ገነት አንተነህ፣ የቦርድ አባል
Genet Anteneh, Board Member


አለበል ደሴ፣ የቦርድ አባል
Alebel Dessie, Board Member


ዶ/ር አስራት ገነት፣ የቦርድ አባል
Dr Asrat Genet, Board Member


ተስፋዬ ጌታቸው፣ የቦርድ አባል
Tesfaye Getachew, Board Member


ሰለሞን ከበረ፣ የቦርድ አባል
Solomon Kebere, Board Member


ግዛው ብዙአየሁ፣ የቦርድ አባል
Gizaw Bizuayehu, Board Member


ወ/ሮ ሠራዊት ስለሺ፣ የቦርድ አባል
Serawit Seleshi, Board Member


መንበረ ታደሰ፣ የቦርድ አባል
Menbere Tadesse, Board Member


መስፍን ተክሉ፣ የቦርድ አባል
Mesfin Teklu, Board Member

# የአብክመ አስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች ቢሮ
# የአብክመ ፖሊስ ኮሚሽን
# የአብክመ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት
# የአብክመ ሚሊሻ ጽ/ቤት

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች ቢሮና በስሩ የሚገኙት የፖሊስ ኮሚሽን፣ የሚሊሽያ ጽ/ቤት እና የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት በጋራ በመሆን የአልማ የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራምን ደግፈው ከማህበሩ ጐን በመቆማቸው ከፍተኛ ደስታ ይሰማቸዋል፡፡

የአስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች ቢሮና የፀጥታ ተቋማቱ የክልላችንን ሰላምና ፀጥታ በማስከበር ለልማትና ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የሚሰሩ ሲሆኑ የክልላችንን ልማት ለማፋጠን የአማራ አቀፍ ልማት ማህበር እስካሁን ላከናወናቸው ተግባራትና በአልማ ጥረት ለተመዘገቡ በርካታ የልማት ውጤቶች ከፍተኛ ክብር አለን፡፡

ይህን ልማት መደገፍና ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ አጋርነትን ማጠናከር አስፈላጊ በመሆኑ፣ አልማ በሚያደርገው ፀረ-ድህነት ዘመቻ አንጻር ህግና ስርአትን በማስከበር ከማህበሩ ጐን በመቆም፣ በተለይም አልማ የሚያደርገው ልማታዊ ጥረት ድህነትን፣ ወንጀልን፣ ግጭትንና ኋላቀርነትን ታሪክ ማድረግ የሚያስችል በመሆኑ አንድ ሆነን እንደ ሺህ ሺህ ሆነን እንደ አንድ ለአልማ የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም መሳካት በጋራ እንረባረብ !!

**በጥረታችን ድህነት ተረት ይሆናል!!**

**አድራሻ**
ስልክ 0582004882
ፋክስ 0582202604
e-mail Asab Millinium@yahoo.com
ፖ.ስ.ቁ. 244